# ሰበር ዜና ! …. ዘለሌ ፀጋስላሴ ግምቦት ሰባትን ለቀቀ (ፅናት አማራ_ስዊድን)

December 19, 2016



የስዊዲን አግ7 ሰብሳቢ ስለ አማራ ባነሱት ጠንካራ ጥያቄ ተከትሎ ከንቅናቄው ለቀቁ ። የስዊድኑ አግ7 ለጊዜው ሰብሳቢ የለውም። በ2002 ምርጫ ኢትዮጵያን ለቆ የተሰደደው፡ ግንቦት ሰባትን በሱዳን እያደራጀ እንደነበር በሃገር መከዳት ክስና ምስክር የቀረበበት፡ የቀድሞው ኢዴአፓ ሊቀመንበር፡ የስዊድን የግምቦት ሰባት ሊቀመንበር ግንቦት ሰባትን በይፋ መልቀቁ እየተወራ ነው።

የንቅናቄው ሊቀመንበር ኖቬምበር 26 በተለያዩ ሃገራት ከሚገኙ አባላቶቹ ጋር ባደረገው ዝግ ስብሰባ ላይ ንቅናቄው በአማራ ህዝብ ላይ እያራመደ ያለውን የጥላቻና የማግለል ተግባር በግልፅ በማስረጃ በመግለፅ ሊቀመንበሩን ያፋጠጡት የአማራ ተወላጁ አቶ ዘለሌ ፀጋ ስላሴ ከስብሰባው በኃላ ከንቅናቄው የማስጠንቀቂያ ፅሁፍ የደረሳቸው ሲሆን ይህንን ተከትሎ በሁኔታው ያዘኑት አቶ ዘለሌ ንቅናቄውን መልቀቃቸውን አሳውቀዋል ። አቶ ዘለሌ በንቅናቄው ዝግ ስብሳባ ላይ የአግ7 አመራሮች ከፍተኛ የአማራ ጥላቻ አለባቸው ። አግ7 በርካታ የኦሮሞ ድርጅቶች መኖራቸውን እያወቀ ከነ ሌንጮ ለታ ድርጅት ጋር ህብረት ሲፈጠር የአማራ ድርጅት አንድ ላይ አልተሳባሰቡም በማለት ህብረት ለመፍጠር አልተቻለም ማለቱ አማራን ማግለል ነው።

በወያኔ ሽግግር ዘመን በአርሲ በሃረር የአማራን ህዝብ የጨፈጨፈ ግለሰብ ከሚመራው ድርጅት ጋር ሲሰራ ለአማራ ህዝብ ያለን ጥላቻ ማረጋገጥ ነው:: የሚል ጠንካራ ሙግት አቅርቦ የነበረ ሲሆን በኖቬምበር 27 የንቅናቄው ገቢ ማሰባሰቢያ ላይ ባደረገው የመክፈቻ ንግግር ይህንኑ አቆም ገልፀ ድርጅቶቹን ነቅፉል በዚህ አቆሙ የተከፉት የንቅናቄው አመራሮች በአስቸኳይ ባደረጉት ስብሰባ አቶ ዘለሌን አፍ ማሳያዣ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው አድርገዋል።

በማስጠንቀቅየው የተበሳጨት አቶ ዘለሌ ለንቅናቄው መልቀቂያ በማስገባት ከንቅናቄው መልቀቃቸው

ታውቋል ። በአሁኑ ሰዓት ስዊዲን አግ7 ሰብሳቢ የለውም ። አቶ ዘለሌ ንቅናቄውን ከወያኔ እጅ ፈልቅቀው ያወጡ ንቅናቄውን ያጠናከሩ ጠንካራ የአማራ ተወላጅ ነበሩ ።

Tsinat Amara